# የገና ሰሞን *(ከተክለ ማርያም ጆሐንሰበርግ)*

(በደቡብ አፍሪቃ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ስላሴ የስደተኞች ቤተ_ክርስቲያን ወቅታዊ ሁኔታ)

ዘመናትን አስቆጥሮ ትንቢትን በነበያት አስነግሮ እኛን ለማዳን አምላክ ሰው ሰው አምላክ የሆነበት የልደት በአል ሊከበር ከአንድ ወር ቀደም ብለን የአባቶቻችን የነቢያ በዓመተ ዓለሙ በዘመነ ኩነኔው የነበሩት ሱባኤ ቆጥረው ከጨለማው ዘመን ከዘመነ ፍዳ በክርስቶስ ደም ለመወጣት ነብያት የፆሙትን ፆም የቻልን አብዛኛዎቻችን በመፆም የነብያቱ በረከት እንዳይለየን አባቶቻችን በቀኖና ከደነገጉልን ሰባት አፆማት መከከል አንዱ ስለሆነ ዘወትርም ሆነ በአገኘናት ሰዓት በተለይ እሁድ በእለተ ሰንበት ሁላችንም አስቀድሰን ለመቁረብ ባንታደልም አስቀድሰን ፀበል ጠጥተን ለነፍሳችን ሐሴት ለስጋችንም እረፍት በረከት በእለተ ሰንበት እናገኛለን አያስቀናም?

በሰው ሐገር በስደት ያውም እንደ ሌሎች ያደጉት ሐገራት ሙሉ ነጻነት በሌለበት ብዙ አስደንጋጭ ዜና በሚሰማበት ሐገር አፍሪቃ ህዝቡ ኑሮውን አሸንፎ በእግዚአብሔር ፈቃድ የራስን ህንጻ ቤተ_ክርስቲያን ገዝቶ በህንጻው አናት ላይ በፍቅር የሚወደን ክርስቶስ የተሰዋበት የመዳናችን ተምሳሌት የነጻነት አርማችን ቅዱስ መስቀል ምልክት ሰቅሎ የሐገራችን ባንዲራ አውለብልቦ የቃል ኪዳኑ ታቦታት ባሉበት ስፍራ አምልኮተ እግዚአብሄር በማድረስ ከአንድዬ ጋርም እለት እለት የልብ የልባችንን ተነጋግረን መልስ የምናገኝበት እምየንም በገባላት ኪዳን መሠረተ ስለ አንች ስለእናቱ ይቅር ይበለን የምናዋይሽን እመ አድርሰሽልን ልጅሽ ይምረን ዘንድ እያልን ምልጃውም እንዳይቀርብን አድርሰን ወደቤታችን የምንሄደው መታደል እኮ ነው:: ታዲያ በዚህ የገና ሰሞን ይህ የእለት ተዕለት የቤ/እግዚአብሄር ምልልሳችን ያስቀናው ዲያቢሎስ ግብሮቹን በተንኮል አሰማርቶ ቤ/ክ ለማፍረስ በስጋቸው አስበው በተንኮል እንዲነሱ ያደረገው::

ክቡራንና ክቡራት አንባቢያን ባለፈው በምንኖርበት ከተማ ጆሀንስበርግ በሚገኘው ቅድስት ስላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የስደተኞች ቤተ_ክርስትያን ለማፍረስ ምእመናንን በተለያየ ዘዴ በአሉባልታ ለመበተን በመሞከር የተለያዩ የግል ስብዕናን በሚነካ የቤተ_ክርስቲያናችንንም የሀይማኖታችንን ስነ ምግባር በሚያጎድፍ መልኩ ያተለያየ የስድብ ወረቀት በአካባቢያችን በመበተንና ሁለት ገጽ ፎርጅድ ዶክመንት አስተዳዳሪው የጻፉት በማስመሰል ለአባ ጳውሎስ ደብዳቤ በመጻፍ በተንኮል አባታችንና ወንድሞቻችንን መወንጀላቸው ይታወቃል::

ከሳሽ ዲያቢሎስ በመሆኑ እነዚህ ግለሰቦች ህዝብንና ምእመናንን ከጎናቸው የያዘ በሚመስል በማስታወቂያ የሃሰት የድረሱልን ህዝባዊ ከንቱ ስብሰባ ጥሪ በማድረግ በቴክኖሎጂ ባቀናበሩት የሀሰት ዶክመንት በመታገዝ በማሰራጨት በጣም በየዋህነታቸውና ደግነታቸው ትእግስታቸውና መንፈሳዊነታቸው ቀርቦ የሚያውቃቸው ባጠቃላይ የሚያውቃቸው የሚወዳቸው አባት ይህን ቤተክርስቲያን በወቅቱ ከነበሩት ምእመናን ጋር በመሆን በአባትነታቸው አስተባብረው መከራ ተቀብለው ለዚህ ያበቁትን ትሁት አባታችን ቆሞስ አባ ሳሙኤልን አምልኮተ እግዚአብሔር ለማከናወን የገዛነውን ህንጻ ቤተ_ክርስቲያን ለአባ ጳውሎስ ሸጡብን (አሳልፈው ሰጡብን) በማለት ስም በማጥፋት በዚህ በቅርብ ያሉት ምእመናን ዕውነቱንና ማንነቱን ቢያውቀውም ምዕመናንን ለማደናገር በምንኖርበት ሳውዝ አፍሪቃና በተለያየ የአለማችን ክፍሎች ይህንን የሀሰት ኢንፎርሜሽን ለወገናችን በማሰራጨት ይባስ ብለው ወቅታዊ ኢንፎርሜሽን ለሀገራችንና ለወገናችን በማድረስ ቀዳሚ ስፍራ በሚይዘው Ethio Media ድህረ ገጽም አውጥቶታል፥በዚህ በትነውትና በህግም አቅርበውት ፎርጀድ መሆኑ የታወቀባቸውን ባለ ሁለት ገጽ ደብዳቤ አንዱን ገጽ ብቻ የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ ጋር የላኩትን ልብ ብላችሁ እንዳስተዋላችሁት ባልስተውም አሁን ግን ሰሞኑን የሆነውን አስገራሚ ሁኔታ ላወጋችሁ ወድጃለሁ መልከም ንባብ::

ታስታውሱ እንደሆነ ከገና በፊት የገና ሰሞን በጃንዋሪ 5 /2010 በህዝብ መገናኛ ደህረ ገፅና ከዚህም ሐበሽ በሚሰራበት የንግድ ተቋማት አከባቢና የመኪና ፓርኪንግ ውስጥ እንዲሁም ሀበሽ በሚኖርበት አከባቢ ፊትለፊት በየግድግዳው ራሳቸውን ከህግ በመሰወር በድብቅ በመበተን ተሰማርተው ቆዩና የጠሩት ህዝባዊ ስብሰባ አድማቸው በቤተ_ክርስቲያኑ በመሆኑ ስብሰባ የጠሩበት ቀን ሲደርስ ስብሰባቸውን ያለከልከይ ለማከሄድ ያመቻቸው ዘንድ አስቀድመው ከክልሉ Jeppe police station በመሄድ የሰበካ

መንፈሳዊ ጉባኤውን ሊቀመንበር ጨምሮ በ4 የቤተ ክርስቲያኗ የሰበካ መንፈሳዊ ገባኤ ኮሚቴዎች ላይ የሀሰት ኬዝ በመክፈት አመቻችተዋል:: እነዚህ የሀሰት ኬዝ የተመሰረተባቸው ኮሚቴዎም ከምሽቱ 10 ሰዓት ገደማ ጉዳዩ እስኪጣራ በፖሊስ ታሰሩ እነዚያም ለተንኮላቸው ጥበብን የተጠቀሙት ግለሰቦች የጠሩት ህዝባዊ ስብሰባ ከምሽቱ 12.00 ሰዓት በመሆኑ ሰዓቱ አይደርስ የለ ደረሰና የግብር አባታቸውን ተግባር ለመፈጸም በ media ሳይቀር ያሰራጩትን ህዝባዊ ስብስባ ሊመሩ እርግጠኛ ሆነው አይናቸውን በጨው ታጥበው በድፍረት ከቅፅረ ቤተ_ክርስቲያን ውስጥ ገቡ ቀድሞውኑ በዚህ የሚገኘው የቤተ_ክርስቲያኗ ምእመናን ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በቅርብ ያለው ህዝብ ነገሩን በንቀትና በቅሌት ቢመለከተውና በጥሪያቸው መሰረት ትኩረት ሰጥቶ የተገኘላቸውም ባይኖርም በአንፃሩ ደግሞ ከላይ በመግቢያየ እንደገለፅኩት ከስራ መልስ ማታ ዘወትር ፀሎት ለማድረስ የሚመጡት ምእመናን በእለቱ የተደረገውን ውስልትና ወንጀል የደብሩን ሊቀመንበር ጨምሮ 4 ግለሰቦች በእነዚህ ሀሰተኞች ተከሰው መታሰራቸውን በእለቱ የሰማ ምእመን በድርጊቱ በመበሳጨት በንዴት ራሳቸውን አፋጦ ግራ ሲያጋባቸው እና ምእመናንም ለሚያውቋቸው ለጓደኞቻቸው ስልክ ሲደዋወሉና ተሰባስበው በጥያቄ ሁሉም አዋክበዋቸዋል እናንተ እነማን ናችሁ? ለምን ስብሰባ ጠራችሁ? ማን ወከላችሁ? ማንን ልትሰበስቡ መጣችሁ? ማንን አስፈቀዳችሁ? በማለት በያአቅጣጫው ሲያዋክባቸው በተንኮል ተደራጅተው በከሳሽነትና በአድመኝነት የተመዘገቡት አጠቃላይ 10 ቢሆኑም በቦታው የተገኙት 5 ነበሩ አምስቱም እየተሸለኮለኩ ነፍሰ ,አውጭኝ ብላው የጠሩጥኝ ስብሰባ ጥለው ወጥተው ጠፉ የገና ሰሞን::

በስደት እቅፍ አድርጋ የሰበሰበችን እናታችን ቤተ_ክርስቲያን ለማፍረስ እኛንም በተለያየ መልኩ ለመፈረካከስ በጀርባችው ሆኖ የላካቸው ማንነታቸው በዚህ የገና ሰሞን ተጋልጦ ስብሰባውን ያለከልካይ የሚያከናውኑ ህዝቡም በተንኮላቸው የሚማረክ መስሏቸው አስቀድመው ለተንኮላቸው እንዲመቻቸው ቤተክርስቲያኗን እንዲያስተዳድሩ በህዝቡ ተመርጠው በሀላፊነት የሚያገለግሉትን ኮማቴዎችም ምሽት 10.00 ሰዓት ላይ በሀሰት ቢታሰሩም ጠዋት በ4.00 ሰዓት ገደማ በነፃ ተፈትተዋል::

የሆነው ሆኖ ከላይ እንደገለፅኩት በግብርና በአመለካከት የሚመስሏቸው በአጠቃላይ 10 ግለሰቦች በተባባሪነትና በከሳሽነት ያስመዘገቧቸው ቢሆንም ፖሊስ ባካሄደው ምርመራ ይህንን የስም ማጥፋት የፎርጀድ ዶክመንት እና የሃሰት ክስ ፖሊስ በቀላሉ የማያየው በመሆኑ ቃላቸውን እንዲሰጡ ቢጠሯቸውም እግሬ አውጭኝ ከህግ በመደበቅና ባለመቅረብ ወደ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው አስተዳደር በመቅረብ የለንበትም ከጉዱ አውጡን በማለት ጓደኞቻቸው ይቅርታ የጠየቁትም በዚሁ የገና ሰሞን ነበር::

በቤተ_ክርስቲያናችን በተፈጠረው ችግር አስመልክቶ በማስታወቂያ በዜና በስልክ በተፈጠረው ሁኔታ እነዚህ ግለሰቦች እያደረሱ ባሉት ጥፋት ለመወያየት እሁድ በ ጃንዋሪ 10/2010 በሰበካ ገባኤው ሊቀመንበር በአቶ ወንድወሰን ጌታቸው ለምእመናን ስለጉዳዩ ገለፃ የተደረገ ሲሆን ምእመናንም በውይይቱ ሰፋ ላለ ሰአት ተወያይቶ ሁሉም የተሰማውን ሀሳብ ያቀረበ ሲሆን በእለቱም የተሰጡት ሀሳቦች ይህንን ተግባር የፈፀሙት ግለሰቦች ለህግ እንዲቀርቡ እንዲደረግ ወይንም የሰበካ ጉባኤው ጉዳዩን ተወያይቶ በሰላማዊ መንገድ በይቅርታ በመፍታት ካየው ጥፋቱን የፈጸሙት ግለሰቦች ንስሀ ገብተው ይህንን ተግባር ለመፈፀም የተነሱበትን አላማና ፎርጅድ ያዘጋጁበትን ምክንያት ገልፀው በህዝብ ፊት ይቅርታ እንዲጠይቁ በመጠቆም እንዲያጋልጡ ምእመናኑ በአጠቃላይ ተስማምተዋል ከዚህም በተጨማሪ በአባታችን በቆሞስ አባ ሳሙኤል የተፈጠረው ፈተና የሀሰት አሉባልታና ከሳቸው ህይወት አንፃር የማይመስል ተግባር በመፈፀሙ ምእመናንን እጅግ ያበሳጨና ያሳዘነ ሲሆን ምእመናን እኚህን መንፈሳዊ አባት በተለያየ ቃላት ይህ የሰይጣን ፈተና በመሆኑ እንዲበረቱልን ጠይቀዋል:: በአጠቃላይ በመፅሀፍ ነገርን ሁሉ በጊዜው በጎ እደረገ እንደሚል በስሙ አባቶቻችን ጉዳዩን ከሰሙበት ጀምሮ ትኩረት ሰጥተው ይህንን ችግር ለመፍታትና በአጋጣሚም እኛን ለመባረክ ይዘውት ከነበረው ቀጠሮ ቀደም ብለው የህይወት ቃል መጋቢያችን መምህር አባ ወልደ ትንሳኤ ከአውስትራሊያ ቀደም በለው በመነሳት የተገኙልን ሲሆን ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ እና ዲያቆን ዶክተር ዮናታንን ይዘው ከካናዳ ድርስ አሰባስቦ ከምንም በላይ ጌታ እግዚአብሔር እነሱን አምጥቶ በእነሱ አገልግሎት እንድንባረክ በማድረጉ ነገሩን ሁሉ ለበጎ ብለን ተቀብለነዋል።

ኢንዲያው ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ደማቅ አቀብበል ተደርጎላቸው የመጡት በዚህ ሁለት ቀን ውስጥ በመሆኑና ያመጡልንም ታላቅ በረከትና ስጦታ እግዚአብሄርም በቅዱሳኑ መታሰቢያ ዘውትር እንዲባርከን ስላደረጉ ከበአል በኋላ እመለስበታለሁ

አሁን ግን አባ ወልደ ትንሳኤ በእኛ ፈተና ምክንያት ያለፕሮግራማቸው ቢገኙም ከዚህ በፊት ለሶስት ጊዜ ስምና ዝናን ጥቅምና ተድላን ሳይፈልጉ ከትራንስፖርት ጀምሮ የተላያየ  የረጅም መንገድ ውጫቸውን ከተለያዩ የክርስቶስ ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም የመንፈስ ልጆቻቸውን ምእመናን በአሜሪካ በአውስትራሊያ በማስተባበር በያለንበት ፈልገው ሰብስበው ዘመናትን በሙሉ በእምነታችን ብቻ  በልማድ እየተመላለስን ስንኖር ብዙ ወገኖቻችንም ሐይማኖታችንን ጠንቅቀው ለማወቅ ባለመታደላችን ብዙ ወገናቻችን በምእራብያውያኑ ሐይማኖት እየተነጠቁ ሲያልቁ እግዚአብሔር እኛን በቤታችን በአባቶቻችን  ንፅህት ቀጥተኛ ሃይማኖት እንድናመልከው ባህላችንንና ስረአታችንን ደግማችንና ቀኖናችን ግልጥልጥ አድርገው ወልደ ዋህድ ብላ ጌታ እየሱስ ክርስቶስን የምታመልከውን በቅድስት ቤተ_ክርስቲያናችን እንድንኮራ አድርገውናል ለመናፍቃንና ለተለያዩ የእምነት ድርጅቶችም ጥያቄዎቻቸው በቂ የሆነ ማስረጃ አስጨጠው  በክርስቶስ ደም የከበረች ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ኮርተን እንድንጠብቃት አድርገውናል። መጽሐፍ ቅዱስን ወንጌሉን ፍትፍት አድርገው የሚሰብኩ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው ፀጋ የተጠቀሙበት ምርጥ ኢትዮጵያዊ እውነተኛ የእግዚአሔር ሰው ህይወታቸው ሁሉ እንደቃሉ የሆነ አባት አባ ወልደ ትንሳኤ በእውነት በእውነት የብዙዎችን አባቶቻችን እድሜ እንደሳቸው ላለ እውነተኛ የወንጌል ሐዋርያ ቢጨምርልን እና አገልግሎታቸውን እንዲያረዝምልን እንጽልያለን እንዲህ ነው አባት ?

በእርግጥ ጥንተ ጠላታችን ዲያቢሎስ እውነተኛን የእግዚሃብሔር ሰውና የክርስቶስን ተከታይ ከሐዋርያት ጀምሮ ለመፈተን እንደማይተኛላቸው ብናውቅም  በእርሳቸው በተለያየ ጊዜ ከሳሽ እሱና የግብር ልጆቹን አሰማርቶ በመሆኑ የስጋን ሐሳብ የሚያከናውኑ ግለሰቦችን እያስነሳ የሚከታተላቸው መሆኑ በሁላቸ ዘንድ ሐሰት አሉባልታው በኛም ዘንድ ዘምቷል ነገር ግን እውነቱ እኝህ ድንቅ የክርስቶስ ሐዋርያ የወንጌል ገበሬ ፈተናውን ሁሉ አሸንፈው ለጤናቸው ሳይጠነቀቁ ዘውትር ለክርስቶስ ወንጌል በመጨህ  አብዛኞቹ  አባቶቻችን የሚፈሩትን እውነት ልክ እንደ እንዳለፍፋት እንድ ብጹእ አቡነ ጎርጎሪዎስ በድፍረት በዚህ ዘመን ተገኝተው መንጋውን ባግባቡ እምነቱን እንዲያውቅ እና እንዲከታተል  የክርስቶስን አዳኝነት እንዲያምን ባጠቃላይ መሰረታዊ እውቀት በማስጨበጣቸው በእኛ ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ መሳሪያ ተብለዋል። ለነገሩ ከሐዋርያት ጀምሮ የወንጌል ሰው ፈተናው ብዙ ነው። ዛሬ ሰው ሲሞት የመሰገናል ይከበራል ልማድ ሆኖብን  እንጂ በዚህ ዘመን ክፉ ትውልድ በመሐበርም በግልም በተንኮል ተደራጅተው ለቤተ_ክርስቲያናችንና ለአገልጋዮቿ ለሊቃውንቱ እንቅፋት በሆኑበት ዘመን እነ ብፁእ አባ ጎርጎሪዎስ ዛሬ ኑረው ቢሆን ከክስ አልፈው ለስቅላት ያበቋቸው ነበር። እናም ወደ ዋናው ጉዳይ ልግባና አባታችን የህይወትን ውሃ ሊያጠጡን ቶሎ በአመቱ መጥተው በቃሉ ሊሞሉን በሰበቡ በመገኘታቸው ይኸው ከማያልቀው በመንፈስ ቅዱስ ከሚፈልቀው በጥሩ አንደበታቸው ከሚነገረው የህይወት ቃል እየተመገብን እንገኛለን መታደላችን ! ! ይህን ሁሉ እድል ማን አየብን ለካስ በሃጢያት አለም ብንኖርም ፍቅር የሆነ አምላካችን ጌታ እግዚአብሔር እስከ ሐጢያታችን የማይተወን ለመለወጥም ጊዜ ይሰጠናል በዘንድሮው የገና ሰሞን ብዙ በረከትን የቸረን ጌታ ከታላቁ መምህራችን አባ ወልደ ትንሳኤ መምጣት ሁለት ሳምንት በኋላ ነው። በዚህ የገና ሰሞን የቃል ኪዳኑን ታቦታ የዘውልን ብፁእ አቡነ መቃርዎስ  ሊያገለግሉን እና ሊባርኩን ነው ዶክተር ዮናታም ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሙያዊ እውቀት ለእኛ ለወገኖቻቸው ለማገልገል ጊዜአቸውን መስዋእት አድርገው የመጡት ስለ ብፁእ አባታችን እና ስለባህላችን አከባበር ሰሞኑን እንደምመለስበት በትህትና እገልፃለሁ። ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ (የአባቶቻችን አምላክ ይባረክ)

እግዚአብሔር አገራችንንና ሐይማኖታችንን ይጠብቅልን ! !